www.abyssinialaw.com




| | |
|---|---|
| 11ኛ አመት ቁጥር 24<br>11th Year No | ባህር ዳር ግንቦት 13 ቀን 1998 ዓ.ም<br>Bahir Dar 20 th May, 2006 |

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHHIOPIA

| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 2.00 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 39/1998 ዓ.ም | Regulation No. 39/2006 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Health Care Financing system Execution, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 39/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሥርዓት ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## Regulation No. 39/2006

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE EXECUTION OF THE HEALTH CARE FINANCING SYSTEMS IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት የሚኖረው የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ የወጣ በመሆኑ፤

በዚህ አዋጅ መሠረት የጤና ክብካቤ ገቢ ማግኛ ስልት የተነደፈ በመሆኑና በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎትን ለማጠናከር እንዲሁም ፍትሃዊና ጥራቱ የተሻሻለ ለማድረግ እንዲቻል ተጨማሪ ሀብት በማፍራትና ወጪን በመጋራት ላይ የተመሠረተ ቀልጣፋና ዘላቂ የጤና አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ይህ በጥቅል የሠፈረው የገቢ ማግኛ ሥርዓት በዝርዝር ደንብ አማካኝነት እንዲተገበር ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 117/1997 ዓ.ም አንቀጽ 36 ድንጋጌዎች በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጤና ክብካቤ ሃብት ማግኛ ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 39/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ "የጤና አገልግሎት"፣ "ነጻ ሕክምና"፣ "ገቢ"፣ "የመጣሻ ክፍያ"፣ "ወጪን የሚሸፍን አካል"፣ "የግል ሕክምና መስጫ ክፍል"፣ "የቅብብሎሽ ሥርዓት"፣ ቤተሰብና

WHEREAS, the Health Service Delivery and Administration Proclamation which shall be implemented in the national Region has been issued;

WHEREAS, a health care financing system has been formulated, pursuant to this proclamation , and it has become necessary to launch dexterous and sustainable health service system, on the basis of additional resource mobilization and cost sharing, so as to strengthen the health service in the Region as well as to make it equitable and better in quality;

WHEREAS, it is found appropriate to enforce this health care financing system, put in general terms through a detailed regulation;

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the power vested in it under the provisions of Art. 58(7) of the revised Regional Constitution as well as Art. 36 of the Health Service Delivery and Administration Proclamation No. 117/2005, hereby issues this regulation.

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Health Care Financing Systems Execution, Council of Regional Government Regulation No. 39/ 2006 ."

### 2. Definition

In this regulation words and phrases such as "Health service", "Fee Waiver", "Revenue" "By-pass fee", "Payment", "Expense Financing Body" "Private wing", "Referral system", "Family" and

www.abyssinialaw.com



ሌሎችም በደንቡ የተካተቱ ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል።

others included in the regulation shall have the same meaning as indicated in the proclamation.

## 3. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ተፈጻሚ የሚሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚተዳደሩ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ላይ ይሆናል።

## 3. Scope of the Regulation

This regulation shall be applied to hospitals and health centers under the jurisdiction of the Amhara Regional Government.

# ክፍል ሁለት
# የሆስፒታሎች አመራርና አሠራር

# PART TWO
# MANAGEMENT AND WORKING PROCEDURES OF HOSPITALS

## 4. ስለ ሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋምና የአባላት ተዋፅኦ

1. በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ሥር ባለ ማንኛውም የመንግሥት ሆስፒታል ተጠሪነቱ ለዚሁ ቢሮ የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ ይቋቋማል፤
2. እያንዳንዱ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ እንደ ሁኔታው ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት አባላት ይኖሩታል፤ አሰያየሙም የፆታ እና የሙያ ተዋፅኦን ባገናዘበ መልኩ ይሆናል፤
3. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላቱ አግባብ ባላቸው የዞን ወይም የከተማ አስተዳደሮች አቅራቢነት በቢሮ ኃላፊው ይሰየማሉ፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው ቢኖርም በሆስፒታሉ ሠራተኞች የተመረጠ አንድ ተወካይ የቦርዱ አባል ይሆናል፤
5. የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የአስረጂነት አቋም ይዞ በድምፅ አልባነት ይሳተፋል።

## 4. Establishment of Hospitals Management Board and Composition of its Members

1. There shall be established a management board which is accountable to the health bureau in any public hospital under the Regional Health Bureau;
2. The management board of each hospital shall constitute at least five and at most seven members, depending on circumstances, and its naming shall take gender and professional mix into account;
3. Chairperson and members of the board shall be named by the Bureau Head upon the recommendation of the relevant zonal or city administration;
4. Notwithstanding the provision of sub-art.3 of this article, one representative of the hospital employees, chosen by the latter, shall be member of the board;
5. The general manager of the hospital shall, having explanatory stand, participate in the board meetings without casting a vote.

www.abyssinialaw.com



## 5. ለቦርድ አባልነት የሚቀርቡ ዕጩዎች

የቢሮ ኃላፊው የቦርድ አባላትን የሚመርጠው በሚከተሉት መስፈርቶች ይሆናል፡-

1. ለጤናው ዘርፍ መሻሻል አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚያስችል የሙያ ብቃትና ልምድ ያለው፣
2. ከግል ጥቅሙ ይልቅ የሆስፒታሉን ጥቅም የሚያስቀድም፣
3. ሆስፒታሉ በተቋቋመበት አካባቢ ነዋሪ የሆነና በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣
4. በቦርድ አባልነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነና ተነሳሽነት ያለው።

## 6. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሆስፒታሉን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤
2. የሆስፒታሉን ስትራቴጂያዊና አመታዊ ዕቅዶች መርምሮ ያፀድቃል፣
3. በቢሮው የሚመደብለትን ጥቅል ዓመታዊ በጀት እና የሆስፒታሉን የውስጥ ገቢ መሠረት በማድረግ የማስፈፀሚያ በጀቱን መርምሮ ያፀድቃል፤
4. የሆስፒታሉን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣
5. የሆስፒታሉ የገቢ ምንጮች የሚዳብሩበትን ሥልት ይቀይሳል፣
6. የቦርዱን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣
7. የሆስፒታሉን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ የሆስፒታሉን ማኔጅመንት አባላት ቅጥርና ዕድገት ያፀድቃል፣
8. ለሦስተኛ ወገኖች በውል የሚሰጡ

## 5. Candidates for Board Membership

The Bureau head shall select the board members on the basis of the following criteria:

1. One having professional expertise and experience enabling him to contribute to the improvement of the health sector,
2. One prioritizing the benefits of the hospital to his personal benefits,
3. One who resides in the environs of the hospital ,and has won favor of the community,
4. One who is voluntary and inspired to serve as a board memer.

## 6. Powers and Duties of the Board

The Board shall, pursuant to the regulation hereby , have the following powers and duties:

1. Oversee and follow up the overall activities of the hospital;
2. Examine and approve the strategic and annual plans of the hospital;
3. Review and approve the execution budget of the hospital on the basis of the block of annual budget allocated to it by the bureau, and of internal revenue of the hospital;
4. Review performance reports of the hospital and then make decision;
5. Devise strategies as to how to expand revenue sources of the hospital;
6. Issue the by-law of the board;
7. Hire the general manager, approve the employment and the promotion of management members of the hospital as well;
8. Determine on the services to be outsourced

www.abyssinialaw.com



አገልገሎቶችን ይወስናል፣ በሆስፒታሉ ሥራ አመራር ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የውል ስምምነት ያፀድቃል፤

9. በሆስፒታሉ ውስጥ ለሚገኙ የኃላፊ የሥራ መደቦች የሚከፈለውን የኃላፊነት አበል ይወስናል፣

10. የሆስፒታሉን የሥራ ክንውን፤ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

11. ቢሮው የሚያወጣቸው መመሪያዎች በሆስፒታሉ ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

12. የግል ሕክምና መስጫ ክፍል ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በማኔጅመንት ተጠንቶ የሚቀርብለትን ጥያቄ፣ የበጀትና የተራፊ ሂሣብ ድልድል መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል።

## 7. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ቦርዱን በሰብሳቢነት ይመራል፣ የቦርዱ ስብሰባዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፤
2. የቦርዱን አጠቃላይ የሥራ ሂደት ይመራል፤
3. ቦርዱን በመወከል አስፈላጊ በሆኑ ስብሳባዎች ላይ ይካፈላል፤
4. ከሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የቦርዱን የመወያያ አጀንዳዎች ይቀርጻል።

## 8. ስለ ቦርዱ የስብሰባና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል ሆኖም

contractually, and approve the contract prepared thereof and presented to it by the hospital management;

9. Determine position allowance payable to head posts available in the hospital;

10. Monitor and supervise the performance, the resource utilization and the service delivery of the hospital;

11. Follow up whether the directives issued by the bureau are properly enforced in the hospital;

12. Examine the demand as studied and submitted by the management as to the establishment of a private wing, allocation of the budget and surplus account, and pass decision thereon.

## 7. Powers and Duties of the Board Chairperson

The chairperson of the board shall have the following powers and duties:

1. Preside over and cause the board meetings to be held in accordance with their schedule;
2. Direct the overall course of action of the board;
3. Participate in necessary meetings representing the board;
4. Outline board agendas for deliberation in consultation with the manager of the hospital.

## 8. Session and Decision Making Procedure of the Board

1. The board shall convene regularly at least quarterly; provided, however, that it may, as it may be necessary, hold its extraordinary

www.abyssinialaw.com



እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል 1/3ኛ የሚሆኑት ጥያቄ ሲያቀርቡ ቦርዱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያካሂድ ይችላል።

2. ስብሰባ ከመካሄዱ ከአንድ ሳምንት ጊዜ በፊት የስብሳባው አጀንዳ ተቀርጾ ለውይይት ከሚቀርቡ አባሪዎች ጋር ለአባላት ይላካል፤
3. የቦርዱ ስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ የሚሆነው ከአባላቱ መካከል 2/3ኛው ሲገኙ ይሆናል፤
4. በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ የተደገፈ ማናቸውም ጉዳይ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል። ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን ሃሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፤
5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-4 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 9. የቦርድ አባላት መብትና ግዴታ

1. ለቦርድ አባልነት የተመረጠ ማንኛውም ሰው በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ መብት አለው፤
2. እያንዳንዱ የቦርድ አባል በመደበኛና በአስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፤
3. የቦርዱ አባላት ለሆስፒታሉ እድገትና ልማት ብቁ አመራርና ድጋፍ መስጠት አለባቸው፤
4. የቦርዱ አባላት በዚህ ደንብ መሠረት ለሚያሳልፉት ውሣኔም ሆነ ለሚፈፅሙት

meetings when the board chairperson happens to call or one-third of the members request for it;

2. A week prior to a board meeting, the agenda of the meeting shall be formulated and sent, together with appendices, to each member;
3. The presence of two-third of the board members shall constitute a quorum;
4. Any proposition supported by a majority vote of the presence shall pass as the decision of the board. Incase of a tie, however, the idea favored by the chairperson shall pass as the decision of the board;
5. Without prejudice to the provisions stated under sub-arts. 1-4 of this article, the board may issue its own detailed executive directive on its meeting and internal working procedures.

## 9. Rights and Obligations of Board Members

1. Any person selected as a board member shall have the right to attendance of the board meetings;
2. Every member of the board is duty bound to attend the regular and the extraordinary meetings;
3. Board members shall provide the hospital with efficient management and support for its growth and development;
4. Board members shall, pursuant to this regulation, have individual and collective

www.abyssinialaw.com



ማናቸውም ተግባር የግልና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፤

5. የቦርዱ አባላት አግባብ ባለው የመንግሥት መመሪያ መሠረት መጠኑ በቢሮው የሚወሰን አበል ይከፈላቸዋል።

## 10. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

1. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤
2. ማናቸውም የቦርድ አባል የሥራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት የግሉ በሆነ ምክንያት ከቦርድ አባልነት መልቀቅ ቢፈልግ ከአንድ ወር በፊት ለቦርዱ ሰብሳቢና ለቢሮ ኃላፊው ማሳወቅ አለበት፤
3. አንድ የቦርድ አባል የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያለመቻሉ ሲረጋገጥና ይኸው በቦርዱ ስብሰባ ላይ ቀርቦ ውሳኔ ሲሰጥበት እንዲሰናበት ጉዳዩ ለቢሮው በጽሁፍ ይቀርባል፤
4. የቦርድ አባላት ያደረጉት አስተዋጽኦ ታይቶ ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፤
5. ቢሮው በጐደሉ አባላት ምትክ ሌሎች አባላትን ይመድባል።

## 11. ስለ ሆስፒታሎች ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የሆስፒታሉን ሥራዎች ይመራል፣ ይከታተላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና

responsibility for the decision they pass, and for any activity they perform;

5. The board members are, based on a relevant government directive, entitled to receive allowance whose amount to be determined by the bureau.

## 10. Duration of Term of Members

1. The term of mandate of board members shall be five years;
2. Where any board member wishes, due to his personal grounds, to resign from membership before the expiry of his term, he shall notify the chairperson of the board and the bureau head thereof a month prior to the date of his resignation;
3. Where it is proved that a board member has failed to discharge his assigned responsibilities, and the board passes decision thereon, the case shall be submitted to the bureau in writing with the intention of sacking him;
4. Each board member may be selected for the second term upon consideration of his performance;
5. The bureau shall assign other members in place of the outgoing ones.

## 11. Powers and Duties of Hospital Manager

The hospital manager shall have the following powers and duties:

1. The general manager of the hospital shall, being the chief executive, follow up and manage its activities in accordance with the general guidelines given to him by the Board of the Hospital;
2. Subject to what is stated in sub-art.1 of this article, the general manager shall

www.abyssinialaw.com



ሥራ አስኪያጁ፦

ሀ/ የሲቪል ሰርቪስ ህግን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሆስፒታሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ለ/ የሆስፒታሉን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲወሰንም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ የሆስፒታሉን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

መ/ ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጁ የሆኑትን የሆስፒታሉን ኃላፊዎች አወዳድሮ በመምረጥ ለቦርድ አቅርቦ ያስፀድቃል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ሆስፒታሉን ይወክላል፤

ረ/ አግባብ ካለው የሆስፒታሉ የሥራ ክፍል የቦርዱን ስብሰባዎች ቃለ-ጉባዔ የሚይዝ ሠራተኛ ይመድባል።

a. hire, administer and fire employees of the hospital in accordance with the basic principles of the civil service law and as per the directives to be issued by the bureau;

b. prepare the action plan and the budget of the hospital, present same to the board and implement them upon approval;

c. prepare the performance and financial reports of the hospital and submit same to the board;

d. select department heads ,on competitive basis , who are accountable to the manager ,and submit same to the board for approval;

e. represent the hospital in all its dealings with third parties;

f. assign an employee who is to take minutes of the board meeting from appropriate section of the hospital.

## 12. የጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊነት

ቢሮው የሚከተሉት ልዩ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. በክልሉ መንግሥት ሥር ለሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ዓመታዊ ጥቅል በጀት እንዲመደብ ያደርጋል፤
2. ሆስፒታሉ የመንግሥትን የጤና ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም መሠረት

## 12. Responsibilities of the Health Bureau

The bureau shall have the following specific responsibilities:

1. Cause the allocation of annual block of budget to hospitals that are under the administration of the Regional Government;
2. Render appropriate assistance to the hospital in its endeavor to carry out its responsibilities in

www.abyssinialaw.com



አድርጎ ለመሥራት በሚያደርገው ጥረት ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤

3. ሆስፒታሉ አስፈላጊ የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስና ገንዘብ የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

line with government health policy, strategy and program;

3. Create conducive environment enabling the hospitals to obtain the necessary human, material and financial resources.

## ክፍል ሦስት
## ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ለሌላ ወገን በውል ስለመስጠት

## PART THREE
## OUTSOURCING NON-CLINICAL SERVICES ON CONTRACT

### 13. መርሆዎች

ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልገሎቶች በሌላ ወገን እንዲከናወኑ በውል የሚሰጡት የጤና ተቋማት ሙሉ አቅማቸውን በሕክምና ነክና በምርምር ሥራዎች ላይ እንዲያውሉ ለማድረግ ሆኖ የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ይፈፀማል፦

1. ወጪን መቀነስ፣
2. ቀልጣፋ የአገልገሎት አሰጣጥ፣
3. የአገልገሎት ጥራትን ማሻሻል።

### 13. Principles

With the intention of making health institutions devote their full capacity to clinical-related and research activities, the outsourcing of non-clinical services shall be effected on the basis of the principles of

1. cost minimization,
2. dexterous service delivery,
3. improvement of service quality.

### 14. መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በሌላ ወገን ይከናወኑ ዘንድ ከመወሰኑ በፊት ከዚህ በታች የተመለከተቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፦

1. በውል የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያቀርቡ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤
2. ለውሣኔ አሰጣጥ የሚያግዝ በቂ መረጃ ማሰባሰብና መተንተን፤
3. የውል አስተዳደር አቅም መፍጠር፤
4. በውል ለሌላ ወገን ሊሰጡ የታሰቡ አገልገሎቶችን ሲያከናውኑ የነበሩ

### 14. Preconditions to be fulfilled

Prior to decision to outsource non-clinical services, the prerequisites indicated herein below shall be met ;hereby to minimize possible negative impacts that may happen due to loss of jobs:

1. Ensure the availability of adequate number competent entities that may supply the services to be outsourced to them contractually;
2. Collect ample information that helps for decision making ,and analyze it;
3. Build contract administration capacity;
4. With regard to the employees who were undertaking the services that are intended to be

www.abyssinialaw.com



ሠራተኞችን አስመልክቶ፦

ሀ/ የተወሰኑት በውል ተቀባዩ አካል በኩል የሥራ ዕድል የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ውል በማዘጋጀት፤

ለ/ እራሳቸውን አደራጅተው በሌላ ወገን እንዲከናወኑ በውል የሚሰጡ አገልግሎቶችን በኮንትራት መልክ የሚወስዱበትን ዘዴ በመፍጠርና፤ ወይም

ሐ/ እንደ ትምህርት ዝግጅታቸውም ሆነ የሥራ ልምዳቸው ክፍት ወደሆኑ ሌሎች የሥራ ቦታዎች በማዛወርና የሥራ ዋስትናቸው ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ከሥራ መፈናቀላቸው ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ጫና መቀነስ፣

outsourced:

a. develop a contract that facilitates for some of them to have job opportunities through the contract taker;

b. create ways whereby those staff members may organize themselves and they take the services to be outsourced in the form contract ; and/ or

c. transfer them to other vacant posts according to their educational level and work experience as well as make their job security sustainable .

## 15. የክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን በጤና ተቋሙ አመራር ሥር ስለማቆየት

በውል ለሌላ ወገን ሊሰጡ ከታሰቡ አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የክትትልና የቁጥጥር ተግባራት በጤና ተቋሙ አመራር ሥር መቆየት ይኖርባቸዋል።

## 15. Maintaining Functions of Monitoring and Controlling Under the Management of Health Institution

Functions of monitoring and controlling associated with services to be outsourced on contract shall be maintained under the management of the Health Institution.

## 16. ስለውል ሰነድ ዝገጅትና ይዘቱ

በውል የሚሰጡ አገልገሎቶችን የሥራ ዝርዝር፣ አገልግሎቶቹን ለመስጠት ተዋዋዩ ሊጠቀምባቸው የሚገባውን ግብዓቶች ዓይነት፣ ጥራትና መጠን እንዲሁም የመጨረሻውን ውጤት የሚያሳይ ግልፅ የውል ሰነድ መዘጋጀት ይኖርበታል።

## 16. Preparation of Contract Document and its Contents

A contract document transparently showing the description of services to be outsourced contractually, and the type, the quality and the quantity of inputs which the contractor may utilize in providing the services as well as the expected outcome shall be prepared.

## 17. በሌላ ወገን ስለሚከናወኑ አገልግሎቶች አመራረጥ

ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልገሎቶች በውል

## 17. Selection of Services to be outsourced

Outsourcing of non-clinical services contractually

www.abyssinialaw.com



ሊሰጡ የሚችሉት የመንግሥትን የዕቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ በመከተል ሆኖ፡-

1. ሌሎች ወገኖች በመስኩ የተሻለ ብቃት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ከዚህ በታች በአንቀጽ 18 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል ጉዳዩን አስመልክቶ በሚወጣ መመሪያ የሆስፒታሉ ሥራ አመራር ቦርድ ወይም የጤና ጣቢያው መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሥራ አመራር ኮሚቴ በሌሎች ወገኖች ቢከናወኑ የበለጠ ውጤት ሊገኝባቸው ይችላል ብሎ የሚያምንባቸውን አገልግሎቶች ለይቶ ሲወስን፤እና
3. በጤና ተቋማቱና በሌላው ወገን መካከል ውሉ የሚፈረመው የጨረታውን ግምገማ ውጤት የሆስፒታሉ ቦርድ ወይም የጤና ጣቢያው መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሥራ አመራር ኮሚቴ ሲያፀድቀው ይሆናል።

## 18. በሌላ ወገን እንዲከናወኑ በውል ስለሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 17 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ ወገን ይከናወኑ ዘንድ በውል ሊሰጡ የሚችሉት ሕክምና ነክ ያልሆኑ የአገልግሎት ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ/ የፅዳት አገልግሎት፣
ለ/ የእጥበት ወይም የላውንደሪ አገልግሎት፣
ሐ/ የምግብ ዝግጅትና አቅርቦት፣
መ/ የቋሚ ንብረቶች ጥገናና እድሳት አገልግሎት፣
ሠ/ የሕትመት አገልግሎት፣
ረ/ የንብረትና የፀጥታ ጥበቃ አገልግሎት፣
ሰ/ የትራንስፖርት አገልግሎት፣
ሽ/ የሕግ አገልግሎት ፣ እና
ቀ/ ሌሎች በቦርዱ ወይም በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሥራ አመራር ኮሚቴ የሚወሰኑ ሕክምና ነክ ያልሆኑ

shall be made on the basis of Government procurement manual:

1. Where it is ensured that other parties have a better efficiency in the sector;
2. Where the management board of the hospital or the management committee of the primary health care unit selects services from among those listed under article 18 herein below, that it believes may produce more result if accomplished by other parties, and decide pursuant to the directive to be issued concerning the issue; and
3. The contract between health institutions and other parties shall be signed where the hospital board/ management committee of Primary Health Care Unit approves the bid analysis result.

## 18. Types of Service to be outsourced on contract

Consistent with the general provisions under Article 17 above, types of non-clinical services that may be considered for outsourcing shall be the following

a. Cleaning services,
b. Wash or laundry service,
c. Preparation and supply of food,
d. Fixed asset maintenance and services ,
e. Printing services,
f. Property and security protection services,
g. Transport services,
h. Legal service, and
i. Other non-clinical services to be determined by the board or the management committee of Primary Health Care Unit.

www.abyssinialaw.com



አገልግሎቶች።

## 19. የውሉ ዘመን

1. ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በሌላ ወገን እንዲከናወኑ በውል የሚሰጡት በቦርዱ ወይም በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት የሥራ አመራር ኮሚቴ የአገልግሎቱን ባህሪና የተቋማቱን ጥቅም ባገናዘበ መልኩ ለሚወሰን የጊዜ ገደብ ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በሌላ ወገን እንዲከናወኑ በውል የሚሰጡበት ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ተጠንቶ በልዩ ሁኔታ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወጣና በሥራ ላይ የሚውል ይሆናል።

## 20. የክፍያ ስልት

በፍትሐብሄር ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአገልግሎቱ የሚከፈለው ዋጋ አንድ ወጥና የማይለዋወጥ መሆኑ በውሉ ውስጥ መመልከት ይኖርበታል።

# ክፍል አራት
# ስለ ግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች አመሰራረትና አሠራር

## 21. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎችን ስለማቋቋም

1. በዚህ ደንብ መሠረት የግል የሕክምና መስጫ ክፍል ሊቋቋም የሚችለው ሆስፒታሉ በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል የሚሰጠውን አገልግሎት በማያስተጓጉል ሁኔታ መሆን

## 19. Duration of contract

1. Non-clinical services shall be outsourced for a time duration to be determined by the board or the management committee of the primary Health Care Unit taking the nature of the service and the benefits of the health institution in to account;
2. Without prejudice to the provisions of sub-art. 1 of the article hereof, a detailed directive whereby non-clinical services to be outsourced on contract shall be especially issued by the Regional Council upon the study of the bureau ,and put into effect.

## 20. Mode of Payment

Without prejudice to the provisions stipulated in the civil code, the service charge shall be stated in the contract as consistent and invariable.

# PART FOUR
# ESTABLISHMENT AND OPERATION OF PRIVATE WINGS

## 21. Establishment of private wings

1. Pursuant to this regulation, a private wing may be established in a way that it does not interrupt the service the hospital renders in the general ward;

www.abyssinialaw.com



ይኖርበታል፤

2. የሕክምናና የምርመራ አገልግሎት ጥራትን በተመለከተ በመደበኛውና በግል ሕክምና መስጫ ክፍል ተጠቃሚዎች መካከል አንዳች ልዩነት አይደረግም፤

3. የግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች መቋቋም በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚሰጠውን የቀጠሮ ጊዜ ለማሳጠር የሚደረገውን ጥረት ማወክ አይኖርበትም፤

4. የግል የሕክምና መስጫ ክፍል ሊቋቋም የሚችለው ጉዳዩን በሚመለከት በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ተጠንቶ የሚቀርበው የውሣኔ ሃሳብ በቢሮው ተገምግሞ ሲፀድቅ ይሆናል።

## 22. በግል የሕክምና ክፍል ስለሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች

ከዚህ በታች የተመለከቱት በግል የሕክምና ክፍል የሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነቶች ናቸው፡-

1. ተኝተው ለሚታከሙ ተገልጋዮች የተመቻቸ የመኝታና የምግብ አቅርቦት፤
2. ከመደበኛ የሥራ ሠዓት ውጪ የሚሰጥ የተመላላሽ ሕክምና አገልግሎት፤
3. በሆስፒታሉ ውስጥ የማይሰጡ የሕክምና አገልግሎቶችን ከሌላ ወገን ጋር በመተባበር በጤና ተቋሙ ውስጥ የማቅረብ ሥራ።

## 23. ስለ ማቋቋሚያ ካፒታል

የግል የሕክምና መስጫ ክፍል፡-

1. ከእርዳታ፣
2. ከልዩ መድሃኒት ቤቶች ትርፍና ከሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ከሚመነጭ ብድር፣
3. ከመንግሥት ከሚገኝ የካፒታል በጀት

2. With regard to the quality of medical and examination services, there shall not be any disparity between that of the beneficiaries of the general ward and the private wings;

3. The establishment of private wings shall not compromise the effort to reduce the waiting times in the general ward;

4. Private wing may be established where the recommendation studied and presented by manager of the hospital concerning the issue is examined and approved by the Bureau.

## 22. Types of services provided in private wings

The following are types of services provided in a private wing:

1. Supply facilitated bed and food services for inpatients;
2. Provision of medical services to outpatients out of regular working hours;
3. Provision of medical services which are not rendered in the hospital, in collaboration with other parties.

## 23. Starting Capital

The private wing may be established with the starting capital drawn from

1. donation,
2. loan sourced from surplus of special pharmacies and internal revenue of the hospital,
3. capital budget support from government, and

www.abyssinialaw.com



ድጋፍ እና

4. እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ምንጮች ተውጣጥቶ ሊቋቋም ይችላል።

4. other sources, as deemed necessary.

## 24. የአገልግሎት ክፍያ አወሳሰን

1. የግል የሕክምና መስጫ ክፍል ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ በሆስፒታሉ ተጠንቶ በቢሮው ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፤
2. የአገልግሎት ክፍያ አወሳሰኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፦

   ሀ/ የሕክምና አገልግሎቱን ጥራት፣

   ለ/ የአገልግሎቱን ወጪ፣

   ሐ/ የግል የጤና ተቋማት ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚጠይቁትን ክፍያ።

## 24. setting Service charges

1. The charge to be paid for the service of the private wing shall be applied where it is studied by the hospital and approved by the bureau;
2. The setting of the service charge shall consider assumptions specified herein below :

   a. quality of medical services,

   b. expense of the services,

   c. the payment which the private health institutions charge for similar services;

## 25. የሥራ ሰዓት

የግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች የሥራ ሰዓት እንደየ አገልግሎቱ እየታየ በቢሮው የሚወሰን ሆኖ በባለሙያዎች መደበኛ አገልግሎቱን በማይጐዳ እና ለአገልግሎቱ አመቺ በሆነ ሁኔታ በዙር ይመደባሉ።

## 25. Working Hours

The working hours of private wings hall be determined by the bureau taking each service situation into account and the assignment of professionals should be in turn in away that it is favorable to and does not adversely affect the activity of the general ward.

## 26. የትርፍ ክፍፍልና አጠቃቀም

ከግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች እንቅስቃሴ የሚገኘው ትርፍ በዋነኝነት በግልና በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ለማሻሻልና የጤና ባለሙያውን የሥራ ትጋት ለማሳደግ የሚውል ሆኖ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 26. Distribution and Utilization of Profits

The profit to be obtained from the activities of the private wings shall due mainly be used to improve the health service being rendered by the private wing and the general ward , and to promote health professionals diligence in their work, the detail shall be determined by directive to be issued by the bureau.

## 27. የሆስፒታሎች ኃላፊነት

የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎችን አሠራር በተመለከተ ሆስፒታሎች የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል።

## 27. Responsibilities of Hospitals

With regard to the working procedures of the private wings, the hospitals shall have the following responsibilities:

www.abyssinialaw.com



1. የግል የሕክምና መስጫ ክፍሎችን ለሕብረተሰቡ ማስተዋወቅ፤
2. ከመኝታ ክፍሎች፣ ከምግብ አቅርቦት እና ከቆይታ ጊዜ በስተቀር ሁሉም ታካሚዎች በመደበኛ እና በግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች የሚያገኙት የሕክምና አገልግሎት ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. በግልና በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች አገልግሎት ለማግኘት የሚኖረውን የቆይታ ጊዜ መግለጽ፤
4. የባለሙያ ምደባ በሚደረግበት ጊዜ በመደበኛና በግል የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሥራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማይኖረው መሆኑን ማረጋገጥ።

1. Publicizing the private wings ;
2. Ensuring that the medical services that all clients obtain from the general ward and the private wing are similar with the exception of accommodation services and waiting time;
3. Notifying the possible waiting time in both the private wings and the general ward;
4. Making sure that assignment of professionals shall not bring about negative influence on the activities of the general ward and the private wings.

## 28. የግል የሕክምና ክፍሎች አስተባባሪ

1. ሆስፒታሉ ለግል ሕክምና ክፍሉ አስተባባሪ ይመድባል፤
2. የግል የሕክምና መስጫ ክፍል የሚተዳደርበት ሁኔታ በሆስፒታሉ የአስተዳደር ሠራተኞች የሚታገዝ ሆኖ፣ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ሥራ አመራር ይሆናል፤
3. አስተባባሪው ከሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ በሚሰጠው የሥራ መመሪያ መሠረት የግል ሕክምና ክፍሉን ሥራ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ ሪፖርት ያቀርባል።

## 28. Coordinator of the Private Wings

1. The hospital shall assign a coordinator to the private wing;
2. The administrative condition of the private wings, being assisted by the hospital administrative employees, shall be accountable to the hospital management;
3. The coordinator shall, in accord with the guideline given to him from the hospital manager, coordinate, follow up and submit report of the performance of the private wings.

# ክፍል አምስት
# የነፃ ሕክምና አገልግሎት

# PART FIVE
# FEE WAIVER SERVICES

## 29. የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች

## 29. Beneficiaries of the Services

www.abyssinialaw.com



የነፃ ሕክምና አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ይሆናሉ፡-

1. የክልሉ ነዋሪዎች ሆነው የቤተሰብ ገቢያቸው መሠረታዊ የኑሮ ወጪን መሸፈን የማይችል ስለመሆኑ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ባሳተፈ መልኩ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች፤
2. የጎዳና ተዳዳሪዎች፣
3. በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉና ክፍለው መታከም የማይችሉ፤ ወይም
4. በጤና ተቋማት የ24 ሰዓት ድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው መክፈል የማይችሉና ወጭውን የሚሸፍን ሌላ አካል የሌላቸው።

Beneficiaries of the free medical services shall be the following:

1. Individuals and families who are residents of the region and whose house-hold income, as is confirmed by the local public officials, with the involvement of local community, cannot afford the expense for their basic livelihood;
2. Street people,
3. Those who are displaced from their residences due to man-made and natural disasters and unable to cover their medical expense; or
4. Those who are beneficiaries of the 24 hours emergency medical service of the health institutions but neither can afford to pay by themselves nor have anyone else to cover the expense for them.

## 30. የነፃ ሕክምና ማስረጃ ዝግጅት

1. በነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ የቤተሰብ አባላትን ስም ዝርዝር የያዘና በቤተሰቡ ኃላፊ ስም የተዘጋጀ ማስረጃ ከዚህ በታች በአንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በቀበሌ አስተዳደር ይሰጣል፣
2. የነፃ ሕክምና ተጠቃሚዎች ዝርዝር በሦስት ቅጂ የሚዘጋጅ ሆኖ
   ሀ/ በጤና ተቋሙ፣
   ለ/ በፈቃድ ሰጪው እና
   ሐ/ የነፃ ሕክምና ፋይናንስን በሚያስተዳድረው አካል እንዲያዝ ይደረጋል።
3. ፈቃድ ሰጪው አካል ለሰጠው የነፃ ሕክምና ማስረጃ ትክክለኛነትና አግባብነት ኃላፊነቱን የሚወስድ ሲሆን ማስረጃው ትክክለኛ ሆኖ ባይገኝ

## 30. Preparation of Fee Waiver Certificate

1. A certificate, listing names of family members who may be beneficiaries of free medical service, and prepared in the name of family head shall be granted by the kebele administration as per the provisions of Article 38 ( 3) below;
2. The list of free medical beneficiaries shall be prepared in three copies and has to be kept by
   a. the health institution,
   b. the certificate granting authority, and
   c. the body administering the fee waiver finance.
3. The certificate granting body shall be responsible for the legality and authenticity of the medical certificate it has granted, and incase the certificate is found falsified, the former shall also be liable to that effect.

www.abyssinialaw.com



ላደረሰው የሥራ አፈፃፀም ጉዳት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

**31. ስለነፃ ሕክምና ማስረጃ የአገልግሎት ዘመን**

1. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ውሳኔ በቀበሌ አስተዳደሮች የሚሰጥ የነፃ ሕክምና ማስረጃ ለሦስት ዓመታት ያገለግላል፤
2. የማስረጃው የአገልግሎት ጊዜ ሲጠናቀቅ በፈቃድ ሰጪው አካል መታደስ አለበት፤

**32. ስለነፃ ሕክምና አገልግሎት ወጪ አሸፋፈን**

1. በጤና ጣቢያዎችና በሆስፒታሎች በተመላላሽና ተኝተው ለሚታከሙ የነፃ ሕክምና ተገልጋዮች በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ተጠንቶ በቁርጥ በሚወሰነው አማካይ የነፍስ ወከፍ የአገልግሎት ክፍያ መሠረት ሃያ አምስት በመቶው ለተቋማቱ እንዲከፈል ይደረጋል።
2. በጤና ጣቢያዎች አማካኝነት ለነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚሰጠው አገልግሎት ወጪ በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር ይሸፈናል፤
3. የቅብብሎሽ ስርዓቱን ተከትሎ በሆስፒታሎች የሚሰጥ የነፃ ታካሚዎች የአገልግሎት ወጪ በክልሉ ጤና ቢሮ ይሸፈናል፤
4. ከሌሎች ክልሎች የሚመጡ እና ከክልሉ ወደ ሌሎች ክልሎች የሚሄዱ የነፃ ታካሚዎች ወጪ አሸፋፈን ጉዳይ ይህንኑ አስመልክቶ በክልሎች መካከል በሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፤

**31. Useful life of Fee Waiver Certificate**

1. A free medical certificate provided by kebele administrations, upon the decision of woreda or city administration, shall be valid for three years;
2. Where the validity period is over, it shall be renewed by the certifying body.

**32. Cost Covering of Free Medical Service**

1. Twenty five percent of the service charge for free medical service beneficiaries , treated as out-patient and in-patient, in health centers and hospitals shall be repaid to the health institutions on the basis of the service charge per capita to be studied and decided guesstimate by the regional health bureau ;
2. The service charge of the fee waiver beneficiaries in health centers shall be covered by the respective city or woreda administrations;
3. The service charge for free of charge medical service beneficiaries in hospitals, through referral system, shall be covered by the Regional health bureau;
4. The service charge coverage for those free of charge beneficiaries, coming from and going to other regions, shall be treated according to the bilateral agreement reached between the two Regions concerning the issue;

www.abyssinialaw.com



5. የነፃ ሕክምና አገልግሎት ወጪ በየሩብ ዓመቱ በጤና ተቋማት አካማኝነት ወጪውን ለሚሸፍኑ አካላት ጥያቄ እየቀረበ ክፍያ ይፈፀማል፤
6. በከተማ አስተዳደር ዙሪያ የሚገኙ ወረዳዎች የነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች የአገልግሎት አሰጣጥ በዙሪያ ወረዳ አስተዳደርና በከተሞች ውስጥ በሚገኙ የጤና ተቋማት መካከል በሚደርስ ስምምነት መሠረት ይፈፀማል።

## 33. የነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ኃላፊነት

ማንኛውም የነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችለውን ማስረጃ በአግባቡ የመያዝ፣ የመጠቀምና ለሌላ ሰው አሳልፎ ያለመስጠት ግዴታ አለበት።

## 34. የአካባቢው ወይም የጎጥ ሕብረተሰብ ኃላፊነት

እያንዳንዱ የነፃ ህክምና አገልግሎት የሚታቀፍበት የአካባቢ ወይም የጎጥ ሕብረተሰብ የነፃ ሕክምና ተጠቃሚዎችን በመለየት፣ አፈፃፀሙን በመከታተልና በመገምገም ሂደት ንቁ ተሳትፎ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## 35. ስለቀበሌ አስተዳደሮች ኃላፊነት

የቀበሌ አስተዳደሮች በዚህ ደንብ አፈፃፀም ረገድ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፦

1. የነፃ ሕክምና አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸውን ነዋሪዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 32 የተመለከቱትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግና የሕብረተሰቡን

5. The expense for fee waiver beneficiaries shall be requested for quarterly by the health institutions, and reimbursed by expense financing bodies;
6. The service delivery to free medical service beneficiaries of those suburb administrations shall be executed in accordance with the agreement to be reached between the suburb administration and the health institutes in those very cities.

## 33. Responsibilities of Fee Waiver Service Beneficiaries

Any free medical service beneficiary shall have the responsibility to properly keep, utilize and not to hand over the free service certificate to somebody else.

## 34. Responsibilities of the Surrounding or Local Community

Each local or surrounding community in which the free medical service beneficiary embraced shall have the responsibility to actively participate in the process of identifying the free medical service beneficiaries ,following up and evaluating the accomplishment.

## 35. Responsibilities of the kebele Administration

For the execution of this regulation, kebele administrations shall have the following responsibilities:

1. Identify those residents who are entitled to fee waiver service, in conformity with the criteria enumerated under Article 32 of this regulation and in such an appropriate way of ensuring community participation;

www.abyssinialaw.com



ተማትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ መለየት፤

2. የነፃ ሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የተመረጡ ነዋሪዎችን ዝርዝር አግባብ ላለው የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ማቅረብ፤
3. ዝርዝሩ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደር ፀድቆ ሲላክለት ለነፃ ሕክምና ተጠቃሚዎች የነፃ ሕክምና ማስረጃ እንዲሰጥ ማድረግ፤
4. የነፃ ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥና የተጠቃሚዎችን ሁኔታ በመከታተል ለወረዳው ወይም ለከተማው አስተዳደር ወቅታዊ የማስተካከያ ሃሳብ ማቅረብ።

2. Submit the list of residents selected to obtain fee waiver service to the relevant woreda or city administration;
3. Cause the granting of free medical service certificate to the beneficiaries where the list is approved and sent to it by the woreda or city administration;
4. Submit duly, following up the condition of free medical service provision and of its beneficiaries, corrective recommendation to the woreda or city administrations.

## 36. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደሮች ኃላፊነት

የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደሮች ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፦

1. የነፃ ሕክምና አገልግሎት ማግኘት የሚችሉ ተጠቃሚዎችን በመለየት ሂደት ለቀበሌ አስተዳደር አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፤
2. በቀበሌ አስተዳደሮች በኩል ተመርጠው የሚላኩ የነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ገምግሞ ማፅደቅ፣ ይህንኑ አግባብ ላላቸው ለቀበሌ አስተዳደሮችና ለጤና ጣቢያዎች ማሳወቅ፤
3. በፀደቀው ዝርዝር መሠረት የነፃ የሕክምና አገልግሎት ወጪውን ለመሸፈን የሚያስችል በጀት መያዝ፣
4. ስለ ነፃ ሕክምና አገልግሎትና ወጪ አሸፋፈን ከጤና ጣቢያዎች ጋር የውል ስምምነት መፈራረም፤
5. ከጤና ተቋማቱ የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ በወረዳው ገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት

## 36. Responsibilities of Woreda or City Administrations.

With regard to the execution of this regulation, woreda and town administrations shall have the following responsibilities;

1. Provide appropriate support to kebele administrative bodies in the process of identifying the beneficiaries of free medical service;
2. Review and approve the list of free medical service beneficiaries selected and sent by kebele administrations, and notify the relevant kebele administrations and health centers of same;
3. Appropriate budget that enables to cover the free medical service expense as per the approved list;
4. Sign a contractual agreement with health centers pertaining to free medical service and its expense coverage;
5. Instruct the woreda finance and plan office to verify and execute the payment so requested by

www.abyssinialaw.com



ተጣርቶ ክፍያ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ማስተላለፍ፤

6. በአቅራቢያቸው ከሚገኙ የጤና ተቋማትና ከቀበሌ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት የሕብረተሰብ ተወካዮች በተገኙበት በዓመት አንድ ጊዜ ስለነፃ ታካሚዎች ፈቃድ አሰጣጥና አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ።

## 37. ስለጤና ተቋማት ኃላፊነት

የጤና ተቋማት በዚህ ደንብ አፈፃፀም መሠረት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፦

1. አገልግሎቱን በክፍያ ከሚያገኙት ሌሎች ተገልጋዮች ባልተለየ መንገድ ለነፃ ታካሚዎች አገልግሎቱን መስጠት፤
2. የነፃ ሕክምና ስለሚሰጥበትና ተጠቃሚዎች ስለሚለዩበት ሁኔታ ለሕብረተሰቡ ትምህርታዊ ቅስቀሳ ማካሄድ፤
3. የነፃ ታካሚውን ወጪ ከሚሸፍነው አካል ጋር ስለአገልግሎት አሰጣጡና የክፍያ አፈፃፀም ውል መፈራረም፤
4. የነፃ ታካሚዎች ዝርዝርና የአገልግሎት ክፍያ መረጃን በማጠናከር ወጪውን ለሚሸፍነው አካል በየሩብ ዓመቱ በማቅረብ የአገልግሎቱን ገቢ መሰብሰብ።

## 38. የጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊነት

በነፃ ሕክምና አገልግሎት ስርዓት ተፈፃሚነት ረገድ ቢሮው የሚከተሉት ልዩ ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፦

1. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች የቅብብሎሽ ስርዓቱን ተከትለው ለሚመጡ የነፃ ሕክምና አገልግሎት ፈላጊዎች የሚሰጠውን የአገልግሎት ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል በጀት መያዝ፤ ጥያቄ ሲቀርብለት ክፍያ መፈፀም፤

the health institutions;

6. Undertake monitoring and evaluation, in collaboration with the health institutions and kebele administrations nearby, concerning the provision of free medical certificate to beneficiaries once a year in the presence of community representatives.

## 37. Responsibilities of Health Institutions

The health institutions shall, pursuant to the execution of this regulation, have the following responsibilities:

1. Provide the service to free medical service beneficiaries with no distinction from those who receive it through payment;
2. Make the community aware the way how free medical service is provided and beneficiaries are identified;
3. Sign a contract with the financer of free medical service on service provision and payment execution;
4. Collect the service charge by compiling the list of free medical service beneficiaries and service charge records, and by submitting same to the financing body quarterly.

## 38. Responsibilities of the Health Bureau

Concerning the execution of free medical service system, the bureau shall have the following specific responsibilities:

1. Allocate budget that enables to cover the charge for the service provided to free of charge service seekers who come to public hospitals of the region through referral system, and execute payment therefore upon request;

www.abyssinialaw.com



2. ለነፃ ሕክምና አገልግሎቱ ሥርዓት ሙሉ ተፈፃሚነት ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
3. የነፃ ሕክምና አገልግሎት በአግባቡ እንዲካሄድ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣትና ተፈፃሚነቱን ማረጋገጥ።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 39. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 40. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ለዚህ ደንብ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

### 41. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ግንቦት 13 ቀን 1998 ዓ.ም
አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

2. Provide appropriate technical support for the full implementation of free medical service system;
3. Issue an implementation directive so as to properly undertake the free medical service and ascertain its application.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 39. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice in contrivance with this regulation shall not apply to matters provided for in this regulation.

### 40. Power to Issue Directives

The bureau may issue directives for the full execution of this regulation.

### 41. Effective Date

This regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 21st day of May, 2006
Ayalew Gobezie
Head of Government of the Amhara National Regional State